# የንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች
# አዋጅ ቁጥር 341/1995 ለማስፈፀም የወጣ መመሪያ 536/2013

በንግድ ሥራ የተሰማሩ ባለሀብቶች በንግድና በዘርፍ ማህበራት በኩል ለራሳቸውና ለሀገራቸው የኢኮኖሚ ዕድገት ሊያስገኙ የሚችሉትን ጠቀሜታ ለማጎልበት እንዲሁም በንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች አዋጅ ቁጥር 341/1995 ለንግድና የዘርፍ ማህበራት የተቀመጡትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስና አዋጁን ለማስፈፀም የሚረዳ መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ ይህ መመሪያ ወጥቷል።

## አንቀጽ 1. አውጭው ባለሥልጣን

የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች አዋጅ ቁጥር 341/1995 አንቀጽ 24 እና 35 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## አንቀጽ 2. ትርጓሜ

"ሚኒስቴር"፣ "ምክርቤት ወይም ምክር ቤቶች"፣ "ክልል"፣ "የዘርፍ ማህበር" እና "ነጋዴ ወይም የንግድ ሥራ" በንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች አዋጅ ቁጥር 341/1995 የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ

## አንቀጽ 3. የዘርፍ ማህበራትን ስለማቋቋም

3.1. የዘርፍ ማህበራት በሀገር አቀፍ ወይም በክልል ወይም በወረዳ ደረጃ በእርሻ ውጤቶች አምራች ነጋዴዎች፣ በፋብሪካ ውጤቶች አምራች ነጋዴዎች፣ በጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራዎች ደረጃ በ ማምረት ተግባር በተሰማሩ ነጋዴዎች እና በማናቸውም የማምረት ተግባር በተሰማሩ ነጋዴዎች ሊቋቋሙ ይችላሉ።

3.2. ሚኒስቴሩ የዘርፍ ማህበራት አባላት ሊሆኑ የሚችሉ አምራች ነጋዴዎችን ከተሰማሩበት የማምረት ተግባር ዓይነት እና ማህበራቱ ሊኖራቸው ከሚችለው የአባላት ብዛት በመነሳት አባላት ሊሆኑባቸው የሚገባቸውን የዘርፍ ማሕበራት ሊወስን ይችላል።

3.3. አደረጃጀታቸው በዚህ መመሪያ የተደነገገውን እስካልተቃረነ ድረስ ተቋቁመው የሚገኙ የዘርፍ ማሕበራት በዚህ መመሪያ መሠረት እንደገና ተመዝግበው የሕግ ሰውነት የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል።

## አንቀጽ 4. የዘርፍ ማህበራት አደረጃጀት

የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክርቤቶች አባላት የሚሆኑ የዘርፍ ማህበራት በአገር አቀፍ ወይም በክልል ወይም በወረዳ ደረጃ የሚደራጁት በሚከተለው አኳኋን ነው።

4.1. ከመነሻው በአገር አቀፍ ደረጃ መደራጀት የሚችሉ የዘርፍ ማህበራት የሚከተሉት ናቸው።

4.1.1. የኢትዮጵያ አታሚዎችና አሳታሚዎች ማህበር

4.1.2. የኢትዮጵያ ቆዳ፣ የጫማና የቆዳ ውጤቶች አምራቾች ማህበር

4.1.3. የኢትዮጵያ ስኳርና ጣፋጮች አምራቾች ማህበር

4.1.4. የኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅና አልባሳት አምራቾች ማህበር

4.1.5. የኢትዮጵያ አትክልት፣ ፍራፍሬና አበባ አምራች ላኪዎች ማህበር

4.1.6. የኢትዮጵያ ብሩምኮርን /Broom Corn/ እና የብሩምኮርን ውጤቶች አምራቾች ማህበር

4.1.7. የኢትዮጵያ መድኃኒትና የህክምና መገልገያዎች አምራቾች ማህበር

4.1.8. የኢትዮጵያ የታክሲደርሚ አምራቾች ማህበር

4.1.9. የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ዕቃዎች አምራቾች ማህበር

4.1.10. የኢትዮጵያ የሜካኒካል ኢንጂነሪንግ እና የመሠረታዊ ብረታ ብረት አምራቾች ማህበር

4.1.11. የኢትዮጵያ የኬሚካል ውጤቶች አምራቾች ማህበር

4.1.12. የኢትዮጵያ የጎማና ፕላስቲክ ውጤቶች አምራቾች ማህበር

4.1.13. የኢትዮጵያ የሥጋ አምራች ሳኪዎች ማህበር

4.1.14. የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎችና መገልገያዎች አምራቾች ማህበር

4.1.15. የኢትዮጵያ ትምባሆና ክብሪት አምራቾች ማህበር

4.1.16. የኢትዮጵያ የመዋቢያዎች (Cosmetics) አምራቾች ማህበር

4.1.17. የኢትዮጵያ የሴራሚክስ እና ብርጭቆና ጠርሙስ አምራቾች ማህበር

4.1.18. የኢትዮጵያ ብረት ነክ ያልሆኑ ማዕድናት አምራቾች ማህበር

4.1.19. የኢትዮጵያ የከበሩ ማዕድናት አምራቾች ማህበር

4.1.20. የኢትዮጵያ የወረቀትና የወረቀት ውጤቶች አምራቾች ማህበር

4.1.21. የኢትዮጵያ ፕራፕሬ፣ ቅባት እህሎች እና ቅመማቅመም አዘጋጅቶ ሳኪዎች ማህበር

4.2. ከመነሻው በክልል ደረጃ መደራጀት የሚችሉ የዘርፍ ማህበራት የሚከተሉት ናቸው::

4.2.1. የጥጥ አምራቾች እና የጥጥ መዳመጫ ባለንብረቶች ማህበር

4.2.2. የአሣ አምራቾች ማህበር

4.2.3. የሰብል አምራቾች ማህበር

4.2.4. የደን ልማት እና ጊንዲላ አምራቾች ማህበር

4.2.5. የጨው አምራቾች ማህበር

4.2.6. የምግብ እና መጠጥ አምራቾች ማህበር

4.2.7. የቡና አጣቢዎችና አበጣሪዎች ማህበር

4.3. ከመነሻው በወረዳ ወይም በከተማ ደረጃ መደራጀት የሚችሉ የዘርፍ ማህበራት የሚከተሉት ናቸው:

4.3.1. የእንጨትና የቀርከሀ ውጤቶች አምራቾች ማህበር

4.3.2. የእህል ወፍጮ ባለንብረቶች ማህበር

4.3.3. የልብስና የሸራ ሰፊዎች ማህበር

4.3.4. የባልትና እና ባሕላዊ የምግብ ውጤቶች አምራቾች ማህበር

4.3.5. የሲልክ እስክሪን እና የማስታወቂያ ህትመት አምራቾች ማህበር

4.3.6. የጋራዥ አገልግሎት ሰጪዎች ማህበር

4.3.7. አነስተኛ የኮንስትራክሽን ዕቃዎች አምራቾች ማህበር

4.3.8. የቤት እንስሳት አርቢዎች እና የእንስሳት ተዋጽኦ አምራቾች ማህበር

4.3.9. የሽመና ውጤቶችና የስጋጃ አምራቾች ማህበር

4.3.10. የብረታብረት ውጤቶች አምራቾች እና የአንጥረኞች ማህበር

4.3.11. የሹራብ አምራቾች ማህበር

4.3.12. የጌጣጌጥ እና የባህላዊ ዕቃዎች አምራቾች ማህበር

4.3.13. የሸክላ ሥራ አምራቾች ማህበር

## አንቀጽ 5. በንግድና በዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች ስለመወከል

5.1. የሚከተሉት የዘርፍ ማህበራት በቀጥታ በከተማ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች አባላት ይሆናሉ::

5.1.1. የልብስና የሸራ ሰፊዎች ማህበር

5.1.2. የባልትና እና ባሕላዊ የምግብ ውጤቶች አምራቾች ማህበር

5.1.3. የሽመና ውጤቶችና የስጋጃ አምራቾች ማህበር

5.1.4. የሹራብ አምራቾች ማህበር

5.2. የሚከተሉት የዘርፍ ማህበራት በቀጥታ የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አባላት ይሆናሉ::

5.2.1. የኢትዮጵያ ስኳርና ጣፋጮች አምራቾች ማህበር

5.2.2. የኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅና አልባሳት አምራቾች ማህበር

5.2.3. የኢትዮጵያ ቆዳ፣ ጫማና የቆዳ ውጤቶች አምራቾች ማህበር

5.2.4. የኢትዮጵያ ሥጋ አምራች ላኪዎች ማህበር

5.2.5. የኢትዮጵያ ~~አትክልት፣ ፍራፍሬ~~ እና አበባ አምራች ላኪዎች ማህበር

5.2.6. የኢትዮጵያ ጥራጥሬ፣ ቅባት እህሎች እና ቅመማቅመም አዘጋጅቶ ላኪዎች ማህበር

5.3. ሚኒስቴሩ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 5.2. የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንዳንድ በአገር አቀፍ ደረጃ የተደራጁ የዘርፍ ማህበራት በአገራችን ኢኮኖሚ ውስጥ ያላቸውን የግብርናና የኢንዱስትሪ ዘርፎችን የማስተሳሰር፣ ለዜጎች የሥራ ዕድል የመፍጠር፣ ኤክስፖርትን በማስፋፋት የውጭ ምንዛሪ የማስገኘት እና በአጠቃላይ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ያላቸውን ሚና ግምት ውስጥ በማስገባት በቀጥታ በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማሕበራት ምክር ቤት አባል እንዲሆኑ መወሰን ይችላል::

## አንቀጽ 6. የዘርፍ ማህበራትና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች ለምስረታ ማሟላት ስለሚገባቸው መስፈርቶች

6.1. የዘርፍ ማህበራት እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች የሚደራጁት በፍትሐብሔር ሕግ ከቁጥር 404 እስከ 482 ባሉት ቁጥሮች ስለማህበራት በተደነገገው እና ስለማህበራት ምዝገባ በወጣው

ደንብ ቁጥር 321/1959 መሠረት ነው፡፡

6.2. በሚኒስቴሩ በሚዘጋጅ የዘርፍ ማህበራት ወይም የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች ሞዴል የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት የዘርፍ ማህበራት ወይም የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች አባላት የመተዳደሪያ ደንብ ተፈራርመውና ከዚሁ ጋር የሥራ አስፈፃሚ አካላት አባላት ምርጫ ቃለ ጉባኤ ከምዝገባ ማመልከቻ ጋር ለሚኒስቴሩ ወይም ለሚመለከታቸው የክልል ቢሮዎች በማቅረብ ይመዘገባሉ፡፡

6.3. ሚኒስቴሩ ወይም የሚመለከታቸው የክልል ቢሮዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት በሚቀርቡላቸው የምዝገባ ማመልከቻዎች መሠረት ማመልከቻዎቹ ከቀረቡ ጀምሮ በ60 ቀናት ውስጥ ምዝገባውን ያጠናቅቃሉ፡፡

## አንቀጽ 7. የዘርፍ ማህበራት የሕግ ሰውነት ስለሚያገኙበት ሁኔታ

7.1. በአገር አቀፍ ደረጃ የተደራጁ የዘርፍ ማህበራት በሚኒስቴሩ ተመዝግበው የሕግ ሰውነት ያገኛሉ፡፡

7.2. በክልልና በወረዳ ደረጃ የተደራጁ የዘርፍ ማህበራት በክልል የሚመለከታቸው ቢሮዎች ተመዝግበው የሕግ ሰውነት ያገኛሉ፡፡

## አንቀጽ 8. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች የሕግ ሰውነት ስለሚያገኙበት ሁኔታ

8.1. በአገር አቀፍ ደረጃ የተቋቋሙ የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች በሚኒስቴሩ ተመዝግበው የሕግ ሰውነት ያገኛሉ፡፡

8.2. በክልል ወይም በወረዳ ደረጃ የተቋቋሙ የዘርፍ ማህበራት በክልል የሚመለከታቸው ቢሮዎች ተመዝግበው የሕግ ሰውነት ያገኛሉ፡፡

## አንቀጽ 9. የሕግ ሰውነት የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

ሚኒስቴሩ ወይም የሚመለከታቸው የክልል ቢሮዎች ለሚመዘግቧቸው የዘርፍ ማህበራት እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች የሕግ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣሉ፡፡

## አንቀጽ 10. ስለንግድና የዘርፍ ማሕበራት ምክር ቤቶች ምዝገባ

የዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ /2/ በየደረጃው በንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክርቤቶች አዋጅ ቁጥር 341/1995 አንቀጽ 29 መሠረት ለሚደረጉ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች ምዝገባ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 11. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ በማናቸውም ጊዜ ይህን መመሪያ ለማሻሻል ይችላል፡፡

## አንቀጽ 12. የመመሪያው የተፈፃሚነት ወሰን እና የሚፀናበት ጊዜ

12.1. ይህ መመሪያ በንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክርቤቶች አዋጅ ቁጥር 341/1995 መሠረት በማናቸውም ደረጃ በሚቋቋሙ ምክር ቤቶች እና የዘርፍ ማህበራት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

12.2. ይህ መመሪያ ከሚያዝያ 15 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር**

በሀገር አቀፍ በክልልና በወረዳ ደረጃ በሚደራጁ የዘርፍ ማህበራት

በአባልነት ሊገቡ የሚችሉ አምራች ድርጅቶች ዝርዝር

1. የኢትዮጵያ አታሚዎችና አሳታሚዎች ማህበር
   - የጋዜጣ የመጽሔት የመፃህፍት እና የመሳሰሉት አሳታሚዎች
   - በማተሚያ ማሽን በወረቀትና በጨርቅ ላይ የሕትመት ሥራ የሚያከናውኑ::
   - የኤሌክትሮኒክስ ህትመት ንግድ ሥራ የሚያካሂዱ
2. የኢትዮጵያ ቆዳ፣ የጫማና የቆዳ ውጤቶች አምራቾች ማህበር
   - በፋብሪካ ደረጃ ቆዳ ማልፋት (Pickeling)
   - በፋብሪካ ደረጃ ቆዳ ማቅለም (Tanning)
   - የጫማ አምራቾች
   - የጫማ የላይኛው ሽፋን (Shoe Uppers) አምራቾች
   - የጫማ ሶል አምራቾች
   - የቆዳ አልባሳትና ሌሎች እንደቦርሳ ሻንጣና የመሳሰሉት የቆዳ ውጤቶች አምራቾች
3. የኢትዮጵያ ስኳርና ጣፋጮች አምራቾች ማህበር
   - ስኳር አምራቾች
   - ከረሜላና የመሳሰሉትን አምራቾች
4. የኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅና አልባሳት አምራቾች ማህበር
   - የድርና ማግ አምራቾች
   - የክር አምራቾች
   - የብርድልብስ አምራቾች
   - የተሰፉ ልብሶች አምራቾች
   - የብትን ጨርቃጨርቅ አምራቾች /ፈትል፡ ሽመናና ማቅለም ወይም ከነዚህ አንዱን የሚሰሩ/
   - የቃጫ ውጤቶች አምራቾች

5. የኢትዮጵያ አትክልት ፍራፍሬና አበባ አምራች ላኪዎች ማህበር
   - አትክልት አምራቾች
   - ፍራፍሬ አምራቾች.
   - አበባ አምራቾች [illegible]
6. የኢትዮጵያ ብሩም ኮርን አምራቾች ማህበር
   - የብሩም ኮርን አምራቾች
   - የብሩም ኮርን ውጤቶች አምራቾች
7. የኢትዮጵያ መድኃኒትና የሕክምና መገልገያዎች አምራቾች ማህበር
   - የመድኃኒት አምራቾች
   - የሕክምና መገልገያ አምራቾች
8. የኢትዮጵያ የታክሲደርሚ አምራቾች ማህበር
   - የታክሲ ደርሚ አምራቾች
9. የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን እቃዎች አምራቾች ማህበር
   - የሲሚንቶና የኖራ አምራቾች
   - የተገጣጣሚ ህንፃ አካላት አምራቾች
   - የኮንስትራክሽን ብረት አምራቾች
   - የእብነበረድ መቁረጥና ማለስለስ ሥራ የሚሰሩ
10. የኢትዮጵያ የኢንጂነሪንግ እና የመሰረታዊ ብረታ ብረት አምራቾች
   - የሚካኒካል ኢንጂነሪንግ ዲዛይንና ሞዲፊኬሽን አገልግሎት አምራቾች
   - የመሠረታዊ ብረታ ብረት አምራቾች
11. የኢትዮጵያ የኬሚካል ውጤቶች አምራቾች
   - የሳሙናና ዲተርጀንቶች አምራቾች
   - የቀለማ ቀለሞች አምራቾች
   - የሙጫና የማጣበሪያ አምራቾች
   - የፀረተባይ አምራቾች

- የጫማ አምራቾች
- በዚህ የዘርፎች ዝርዝር ውስጥ ያልተካተቱ የኬሚካሎች አምራቾች

12. የኢትዮጵያ የጎማና ፕላስቲክ ውጤቶች አምራቾች
    - የተሸከርካሪ ጎማ አምራቾች
    - አሮጌ የተሸከርካሪ ጎማ እንደገና ሰሪዎች (tyre retreading)
    - ሌሎች የጎማ ውጤቶች አምራቾች
    - የፕላስቲክ እቃዎች አምራቾች
    - የፕላስቲክ ከረጢቶች አምራቾች
    - የፖሊፕሮፕሊን ጆንያ አምራቾች
    - የእስፖንጅ ፍራሽ አምራቾች

13. የኢትዮጵያ ስጋ አምራች ላኪዎች ማህበር

    የከብት የበግ የፍየል የግመል የአሳማ የዶሮ የአሳ ወዘተ... ስጋ በፋብሪካ ወይም በቄራ አዘጋጅተው ወደ ውጭሀገር የሚልኩ

14. የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎችና መገልገያዎች አምራቾች ማህበር
    - የቴሌቪዥን አምራቾች
    - የኤሌክትሪክ ዕቃዎች አምራቾች /ለምሳሌ አምፑል የኤሌክትሪክ ምጣድ/
    - የብየዳ መሣሪያዎች አምራቾች
    - የውሃ ፓምፖች አምራቾች
    - የኤሌክትሪክ ጄኔሬተሮች አምራቾች
    - ሌሎች የኤሌክትሪክና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች አምራቾች

15. የኢትዮጵያ ትምባሆና ክብሪት አምራቾች ማህበር
    - የትምባሆ ቅጠል አምራቾች
    - የሲጋራ አምራቾች

- የክብሪት አምራቾች

16. የኢትዮጵያ የመዋቢያዎች (Cosmetics) አምራቾች ማህበር
    - የፀጉርና የሰውነት ቅባት አምራቾች
    - የሽቶ አምራቾች
17. የኢትዮጵያ የሴራሚክስ እና ብርጭቆና ጠርሙስ አምራቾች ማህበር
18. የኢትዮጵያ ብረት-ነክ ያልሆኑ ማዕድናት አምራቾች ማህበር
19. የኢትዮጵያ የከበሩ ማዕድናት አምራቾች ማህበር
    - የወርቅ፣ የብር የኦፓል የዕንቁና የመሳሰሉት አምራቾች
20. የኢትዮጵያ የወረቀትና የወረቀት ውጤቶች አምራቾች ማህበር
    - የፐልፕ አምራቾች
    - የወረቀት አምራቾች
    - የመፀዳጃ ወረቀቶች አምራቾች
    - የካርቶኖችና የወረቀት ማሸጊያዎችና መያዣዎች አምራቾች
    - ከወረቀት የሚሰሩ የፀሐይ መከላከያ ኪፖች እና የመሳሰሉት አምራቾች
21. የኢትዮጵያ ጥራጥሬ ቅባትእህሎች እና ቅመማቅመም አዘጋጅቶ ላኪዎች ማህበር
    - ጥራጥሬ ቅባትእህሎች እና ቅመማቅመም አዘጋጅተው የሚልኩ
    - የቅመማቅመም ቀማቂዎች አዘጋጅተው የሚልኩ
    - የቅባትእህሎች አምርተው የሚልኩ
22. የጥጥ አምራቾች እና የጥጥ መዳመጫ ባለንብረቶች ማህበር
23. የአሳ አምራቾች ማህበር
24. የሰብል አምራቾች ማህበር /ከአትክልት ፍራፍሬና አበባ በስተቀር ማናቸውንም ሰብሎች የሚያመርቱ/
25. የደን ልማት እና ጎንዴላ አምራቾች ማህበር

- ከዛፍ ግንድ የእንጨት መሰንጠቅ ስራ የሚሰሩ እና ግንዲላና ጣውላ የሚያመርቱ
- የደን ልማት የሚያካሂዱ
- የቺፕውድ የሚያመርቱ
- የኮምፔንሳቶ (Ply wood) የሚያመርቱ

26. የፈጪው አምራቾች ማህበር
27. የምግብና መጠጥ አምራቾች ማህበር
    - የቢራ ሌሎች የአልኮል መጠጦች፡ የለስላሳ መጠጦች፡ የማዕድን ውሃዎች፣ በውሃ የሚበረዙ ለስላሳ መጠጦች፣ የታሸጉ የፍራፍሬ ጭማቂዎች የመሳሰሉትን አምራቾች
    - የዱቄት፣ ፓስታ፣ መኮሮኒ፣ ኬክ፣ ዳቦ፣ ብስኩት፣ የአቾሎኒ ቅቤ፣ ማርጋሪን፣ ማርማላት፣ የምግብ ዘይት እና የመሳሰሉት አምራቾች
28. የቡና አጣቢዎችና አበጣሪዎች ማህበር
    - ቡና በማጠብና በማበጠር ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚያቀርቡ
29. የእንጨትና የቀርከሃ ውጤቶች አምራቾች ማህበር
    - ከእንጨትና ከቀርከሃ የሚሰሩ ልዩ ልዩ ዕቃዎች አምራቾች
30. የእህል ወፍጮ ባለንብረቶች ማህበር
    - የእህል ወፍጮ ኖሯቸው የእህል መፍጨት ሥራ የሚሰሩ
31. የልብስና የሸራ ሰፊዎች ማህበር
    - ራሳቸው ከልብስ እና ከሸራ ጣቃ ልብስ እና ሌሎች ተመሳሳይ መገልገያዎችን የሚሰፉ
32. የባልትና እና ባህላዊ የምግብ ውጤቶች
    - ቅመማቅመም፡ በርበሬ፡ ሽሮ፣ እንጀራ፡ ቆሎ፣ ጭኮ፡ በሶ፡ የመሳሰሉትን አዘጋጅተው የሚሸጡ

33. የሲልክ እስክሪን እና የማስታወቂያ ሕትመት አምራቾች ማህበር

- በሲልክ እስክሪን ሕትመት ሥራ የተሰማሩ
- የማስታወቂያ ሰሌዳዎችን /ላይትቦክስ ቢልቦርድ ሌሎች ተለዋዋጭ የማስታወቂያ ሰሌዳዎችን / የሚሰሩ
- በጨርቅ ላይ ማስታወቂያዎችን የሚያዘጋጁ

34. የጋራዥ አገልግሎት ሰጪዎች ማህበር

- የተሽከርካሪዎች ጥገና ሥራ የሚያከናውኑ
- የመኪና ቀለም የሚቀቡ
- የተሽከርካሪ ቅርጾችን የሚለውጡ

35. አነስተኛ የኮንስትራክሽን ዕቃዎች አምራቾች ማህበር

- የድንጋይ የገረጋንተ፣ የአሸዋ እና የመሳሰሉት አምራቾች
- የጠጠር መፍጨት ሥራ የሚያከናውኑ
- እንደጡብ ብሎኬትና ቱቦዎች የመሳሰሉትን የሚያመርቱ
- ሴራሚክ ያልሆኑ የወለል ንጣፎች አምራቾች

36. የቤት እንስሳት አርቢዎች እና የእንስሳት ተዋጽኦ አምራቾች ማህበር

- ንብ አናቢዎች
- የወተት ከብቶች አርቢዎች
- የስጋ እንስሳት አርቢዎች /በግ፣ ፍየል፣ አሳማ፣ በሬ/
- የእንስሳት መኖ አምራቾች
- የዶሮና የእንቁላል አምራቾች

37. የሽመና ውጤቶችና የስጋጃ አምራቾች

- ከጥጥ ፈትል ባህላዊ ልብስና ከሌሎች በፋብሪካ የተሰሩ ክሮች ልብሶችና የመጋረጃ ጨርቆችን የሚሸምኑ
- የስጋጃ ሥራ የሚሰሩ

38. የብረታ ብረት ውጤቶች አምራቾች እና አንጥረኞች ማህበር

- ከብረታብረት ልዩ ልዩ መገልገያዎችን /በር መስኮት የቤት ዕቃዎች/ የሚሰሩ
- ከወርቅ፣ ከብር፣ ከነሐስ ልዩ ልዩ ጌጣጌጦችንና መገልገያዎችን /መስቀሎችን ፅናጽል ደወል/ የሚሰሩ

39. የሽሩብ አምራቾች ማህበር

- በፋብሪካ ከተሰሩ ክሮች ሽሩብ ቀሚሶች ከፍያዎች ፎጣዎች በማሽን ወይም በሌላ ዘዴ የሚያመርቱ

40. የጌጣጌጥ እና የባህላዊ ዕቃዎች አምራቾች ማህበር

- የባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች አምራቾች
- የጌጣጌጥ ዕቃዎች፣ የቆዳ ላይ ስዕሎችን፣ የጨርቅ ላይ ስዕሎችን፣ የአለላና ስንደዶ ስራዎችን የመሳሰሉትን የሚሠሩ
- ከቆዳ ከቅልና ከሌሎች ዕጽዋት የሚሰሩ ጌጣጌጦችን የሚሰሩ

41. የሸክላ ሥራ አምራቾች ማህበር

- ከሸክላ የቤት ውስጥ መገልገያዎችንና ጌጣጌጦችን የሚሰሩ